# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦክቶበር 21-31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከኖቬምበር 1-10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2021
አዲስ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
| --- | --- |


እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ........ 4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 4

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ........ 5

በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 5

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታበውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 6

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው የአየር ........ 7

ሁኔታ አዝማሚያ ........ 7

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 9


# ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በአንዳንድ የመካከለኛዉና የምስራቅ ደጋማ ስፍራዎች ላይ የለሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት በተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከ05 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በቡኢ 3.6፣ በደብረብርሃን 2.6 እና በሀገረማርያም 3.4 በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል ለደመና መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡባዊ አጋማሽና ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በመፈጠራቸዉ በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በጥቂት የምዕራብ ጎጃም፣ በመተከልና በአሶሳ፣ በቄለምና ምዕራብ ወለጋ፣ በጅማ፣ በኢሉባቦር፣ በባሌ፣ በጉጂና ቦረና፣ በሸካ፣ በከፋ፣ በጋሞ፣ በጎፋ፣ በቤንች ማጂ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በሰገን ህዝቦች እና በጥቂት የቆራሂ ጀረር ዞኖች ላይ ለተወሰኑ ቀናት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተዝግቧል፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በቄለምና ምዕራብ ወለጋ፣ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በጥቂት የምስራቅ ወለጋ፣ በጉጂና ቦረና፣ በአንዳንድ የምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ እንዲሁም ባሌ፣ በጥቂት የሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን ወሎ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሁሉም ዞኖች፣ በአገዉ አዊና ጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ በሸካና ከፋ፣ ቤንች ማጂ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ሰገን ህዝቦች፣ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የአፍዴር፣ ሊበንና ፊቅ ዞኖች ላይ ከ5-61 ሚሜ የሚደርስ ከ2-8 ቀናት ያህል የሚደርስ ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሁሉም ዞኖች፣ በጥቂት የሸካና ጋሞ፣ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሸዋ እና ሰሜን ጎንደር ኪስ ቦታዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የኦክቶበር የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ (dry moisture condition) በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አመዝኖ እንደነበረ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የሌሊቱ እና የማለዳው ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ አካባቢዎች ላይ አንጻራዊ መጠናከር እንዲኖረው አስተዋጽዖ የነበረው ሲሆን፣ ከዚሁ ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ጣቢያዎች ላይ በተለያዩ ቀናት የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት ከ 5 ዲግሪ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። በሌላ በኩል በተወሰኑ የደቡባዊ አጋማሽና የምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለእርጥበት መጨመር አመቺ ሁኔታ የነበረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበታማ ሁኔታ እንደነበራቸው የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በአጠቃላይ ባሳለፍናቸው የኦክቶበር የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት የተስተዋለው የአየር ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘው የግብርና እንቅስቃሴ ላይ የተለያየ ተጽዕኖ እንደነበረው መገንዘብ ይቻላል። በተለይም ደረቅ ፀኃያማና ነፋሻማ የነበረው የአየር ሁኔታ ለደረሱና በመድረቅ ሂደት ውስጥ ለሚገኙ ሰብሎች አዎንታዊ ሚና የነበረው ቢሆንም በሌላ መልኩ በተለለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና እድገታቸውን ላላጠናቀቁ እንዲሁም ተጨማሪ እርጥበት ለሚያስፈልጋቸው የመኸር ጊዜ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች አሉታዊ ጎን ነበረው። በአንጻሩ በደቡባዊ አጋማሽና በምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተመዘገበው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት በተለይም እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች ገንቢ ሚና የነበረው ሲሆን በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተለያዩ የግብርና እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን ዕድል የፈጠረ ከመሆኑም በላይ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል ገንቢ ሚና ነበረው። ሆኖም ግን አስቀድመው ተዘርተው እድገታቸውን ለጨረሱ እና በመድረቅ ሂደት ውስጥ ለሚገኙ አንዳንድ የመኸር ወቅት ሰብሎች የነበረው እርጥበታም ሁኔታ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታበውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 21-31 ኦክቶበር 2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የተሻለ እርጥበት በደቡብ ምእራብና በደቡብ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል፡፡ ይህንን ተከትሎ የመካከለኛው ባሮአኮቦ፣ በጥቂት የላይኛው አባይ፣ የባሮአኮቦና ኦሞጊቤ አዋሳኝ ቦታዎች፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ኦሞ ጊቤና የመካከለኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል$ በሌላ በኩል መጠነኛ እርጥበት በተለይም የላይኛውና የመካከለኛው ገናሌዳዋ ያገኙ ሲሆን፤ የተቀሩት በአብዛኛው የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅና የመካከለኛው ተፋሰሶች በደረቅ ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ" ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ቢሆንም፣ አልፎ አልፎ በሉት ቀናት የደመና ሽፋን በአንዳንድ በምዕራብ አጋማሽና በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በአንፃራዊ ሁኔታ ሊቀንስ እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

በዚህም መሰረት <u>ከኦሮሚያ ክልል የወለጋ ሁሉም ዞኖች፣ ኢሉአባቦራ፣ እንዲሁም የጉጂ፣ የቦረና፣ የአረሲ እና ባሌ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳና የከማሺ ዞኖች፤ ከአማራ</u>

ክልል የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ሕዝቦች፣ የጌዲዮ፣ የጋሞ እና የጎፋ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የሚገኙት አፍዴር እና የሊበን ዞኖች በተለያዩ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገራችን አካባቢዎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የሚስተዋል ሲሆን፤ በሌላ መልኩ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምስራቅ እንዲሁም በመካከለኛው አካባቢዎች ላይ መጠነኛ የሆነ እርጥበት የሚያገኙበት ጊዜ ነው፡፡

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በሚቀጥሉት የኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው የበጋው ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በተለይም የመኸር ሰብል ለሚሰበስቡና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለሚያከናውኑ አካባቢዎች አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች ይህንኑ ምቹ ሁኔታ ከግምት በማስገባት የደረሱ ሰብሎችን በአግባቡና በጊዜው እንዲሰበስቡ ይመከራሉ፡፡ እንዲሁም አልፎ አልፎ በአንዳንድ በምዕራብ አጋማሽና በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን ከመኖሩ ጋር የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በአንፃራዊ ሁኔታ ሊቀንስ እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በአንፃሩ ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በተለይም የደቡባዊ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በተለያዩ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበት በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበጋ ወቅት ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት በአንዳንድ የምዕራብ አጋማሽና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍል በሚገኙት ተፋሰሶች ላይ የመጠኛ እርጥበት እንደሚኖራቸውና በተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደግሞ ደረቅና ፀሓያማ ሁኔታ እንደሚስተዋል ትንበያው ያመለክታል፡፡ ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ገናሌዳዋ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ የታችኛው ኦሞጊቤ፣ አጋዴን፣ የአባይ የላይኛውና የታችኛው አጋማሽ እንዲሁም የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች አነስተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በመሆኑም በእነዚህ ተፋሰሶች ላይ የሚገኘው እርጥበት የውሃ ሀብት ግብዓትን እንዲጨምር አስተዋፆ ከማድረጉም በላይ በተለያየ ዘዴ ውሃን በመሰብሰብ ዘለቄታ ጥቅም እንዲኖረው ለማድረግ ያስችላል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ ሁኔታ እንደሚስተዋል ይጠበቃል።